# የገላቲያ ጥናት

**የጥናት ክፍል፡ ገላቲያ ምዕራፍ 3**

| መመልከት | መተርጎም | ማዛመድ |
|---|---|---|
| ምን አያለሁ? | ምን ማለቱ ነው? | እንዴት ሊተገበር ይቻላል? |

**ርዕስ፡ በእምነት ስለሚገኝ ፅድቅ፡፡**

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ጳውሎስ በእምነት ስለሚገኘው ፅድቅ ከራሱ ህይወትና ከቅዱሳ መፃህፍት መረጃ እያቀረበ እንዴትም  በሰው ሕይወት ተግባራዊ መሆን እነደሚቻል ያስረዳቸዋል፡፡

በዚህ ክፍል ውስጥ ተቃራኒ የሆኑ ቃላትን ለምሳሌ (**<u>በረከት↔መርገም</u>**) በተደጋጋሚ የተጠቀሱ ቃላትን እና ባጠቃላይ የክፍሉ ዋና ሀሳብ እና ያያችሁትን ዋና ዋና ነገሮች ዘርዝሩ፡፡

______________ ↔ ______________ ፣ ______________ ↔ ______________

______________ ↔ ______________ ፣ ______________ ↔ ______________

______________ ↔ ______________ ፣ ______________ ↔ ______________ **<u>ወንድ</u>** ↔ **<u>ሴት</u>**

***የመወያያ ጥያቄዎች፡-***

1. ጳውሎስ የገላቲያ ሰዎችን ለጠየቃቸው ጥያቄ ምን አይነት ምላሽ የሚሰጡት ይመስላችኋል?
2. ክርስቶስ በፊታቸው ተሰቅሎ ሲል ምን ማለቱ ነው?
3. ለአብርሃም  በሮሜ ውስጥ 9 ጊዜ በገላቲያ ውስጥም 9 ጊዜ እርሱም ምዕራፍ 3 ላይ 8 ጊዜ 4 ላይ 1 ጊዜ ተጠቅሷል ከምን ጋር ተያይዞ እንደሆነ ተነጋገሩ፡፡
4. ሕግ የሚለው ምንን ያሳያል የህግ ድካም ወይም ማደረግ የማይችላቸው ነገሮች ምንድርን ናቸው?
5. ጳውሎስ ..."**ናችሁ**" የሚላቸውን ቢያንስ 5 ነገሮችን ዘርዝሩ፡፡ ለምሳሌ ቁጥር 29 **<u>ወራሾች</u>** ናችሁ።

## ከግል ሕይወት ጋር ማዛመድ እና መተግበር (Application)

6. ክርስቶስን መልበስ እነዴት ነው እንዴትስ በህይወቴ ይገለጣል?  ከሮሜ 13፡ 8-14 ጋር ተመልከቱ
7. ድነትን (salivation) በተመለከተ በክርስቶስ የተደረጉልን የማናስተውላቸው ነገሮች  ምን ይሆን?
8. ክርስቶስ በዓይናችሁ ፊት እንደተሰቀለ ሆኖ ተስሎ እየታየ ነው የማይታይ ከሆነስ ምን እናድርግ?
9. በመንፈስ የተጀመረ ነገር እና ወደ ሥጋ እየተቀየረ ያለ ነገር ይኖር ይሆን እንዴት ይፈተሻል?
10. በእምነት ስለሚገኝ ፅድቅ (ስለወንጌል እውነት) አእምሮአችን ምን ያህል ተቃኝቷል፡፡

በመጨረሻም በዛሬ ጥናት መንፈስ ቅዱስ በተለየ መንገድ አስተምሮኛል የምትሉትን ለቡድናችሁ አካፍሉ፡፡